የአድልዎ አቤቱታ መቅረብያ ቅጽ

ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች የአንላይን መረጃውን ምንም አይነት ችሎታ ወይም ቴክኖሎጂ ሳይገድብ ለሁሉም ሰው ተደራሽ እና ጥቅም ላይ እንዲውሉ ለማድረግ ቁርጠኛ ነው።የድር ተደራሽነት መመሪያዎችን እና ደረጃዎችን ማሟላት ለማሻሻል በተከታታይ እየሰራን ያለነው ቀጣይ ሂደት ነው።

ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ለተደራሽነት ምቹ የሆኑ ሰነዶችን ለመለጠፍ ጥረት የሚያደርግ ቢሆንም፣ በየአንዳንድ ሰነዶች ባህሪ እና ውስብስብነት ምክንያት፣ተደራሽ የሆነ የሰነዱ ስሪት ላይገኝ ይችላል።በእነዚህ ውስን ሁኔታዎች፣ዲስትሪክቱ በተመሳሳይ መልኩ ውጤታማ የሆነ አማራጭ ተደራሽነትን ያቀርባል።

ስለዚህ ሰነድ ጥያቄዎች እና ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣እባክዎን የሚከተሉትን ያነጋግሩ:

- ተማሪዎች፣ወላጆች/አሳዳጊዎች እና የሕዝብ አባላት: oscr@seattleschools.org
- የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ሠራተኞች: hreeoc@seattleschools.org

የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የልዩነት/የአድልዎ አቤቱታ ቅጽ(Seattle Public Schools Discrimination Complaint Form) ልዩነት/አድልዎ ወይም ትንኮሳን ሪፖርት ለማድረግ የሚያገለግል ባለ አራት ገጽ ሰነድ ነው።ይህ ቅጽ መመሪያዎችን፣የመገናኛ አድራሻዎችን፣እንዲሁም ድርጊቶችን ለመግለጽ፣የግል መረጃዎችን ለመስጠት እና የምስክሮችን ዝርዝር ለማስፈር የሚያስችሉ ክፍሎችን ያካትታል።የግልግል (የማስታረቅ) አማራጮች እና ተጨማሪ ደጋፊ ሰነዶችም አብረው ሊያያዙ ይችላሉ።

የሲያትል የህዝብ ት/ቤቶች
የአድልዎ አቤቱታ ማቅረቢያ ቅጽ

የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ፖሊሲ በጾታ፣በዘር፣በዕምነት፣በቆዳ ቀለም፣በሃይማኖት፣በትውልድ ሐረግ፣ በብሔራዊ መነሻ፣በእድሜ፣በነርቭ ልዩነት (neurodivergence)፣በጾታዊ ዝንባሌ (የጾታ መገለጫን ወይም ማንነትን ጨምሮ)፣በእርግዝና፣በጋብቻ ሁኔታ፣በአካላዊ ገጽታ፣በማንኛውም የስሜት ህዋሳት፣የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳት መኖር፣በክብር በተሰናበተ የቀድሞ ወታደር ወይም ወታደራዊ ሁኔታ፣ቤት-አልባነት፣በብሔረሰብ፣በስደት ወይም በዜግነት ሁኔታ፣ወይም በሰለጠነ ውሻ ወይም ረዳት እንስሳ አጠቃቀም ላይ የተመሠረተ ማንኛውንም ዓይነት ልዩነት/አድልዎ በጥብቅ ይከለክላል።

<u>አድልዎ ምንድን ነው?</u> ልዩነት/አድልዎ (Discrimination) ማለት አንድ ሰው ወይም ቡድን ጥበቃ የሚደረግለት መደብ (protected class) ተብሎ በሚታወቀው ቡድን አካል በመሆናቸው ምክንያት የሚፈጸምባቸው ሕገ-ወጥ አያያዝ ነው።ልዩነት/አድልዎ አንድ ሰው ጥበቃ ከሚደረግለት ክፍል አባል በመሆኑ ምክንያት በተለየ ሁኔታ ማስተናገድ ወይም በአንድ ፕሮግራም፣አገልግሎት ወይም እንቅስቃሴ ውስጥ እንዳይሳተፍ መከልከል ወይም የአንድን ሰው የአካል ጉዳት አለማስተናገድን (ለጉዳቱ ተስማሚ ሁኔታዎችን አለመፍጠርን) ሊያካትት ይችላል።አድልዎ የተሞላበት ትንኮሳ (Discriminatory harassment) ማለት ጥበቃ በሚደረግለት መደብ ላይ የተመሠረተ የቃላት ወይም የአካል ትንኮሳ ነው።

<u>ጥበቃ የሚደረግለት ክፍል?</u> ጥበቃ የሚደረግለት ክፍል የጋራ ባህሪያትን የሚጋሩ እና በፌዴራል፣በክልል ወይም በአካባቢው ህጎች ከአድልዎ እና ከትንኮሳ የተጠበቁ የሰዎች ቡድን ነው። በሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ጥበቃ የሚደረግላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች (Protected classes) የሚባሉት፣ከላይ በአድልዎ መከላከያ መግለጫው ላይ የተጠቀሱት እንደ ጾታ፣ዘር እና የመሳሰሉት ቡድኖች ናቸው።

<u>ስለ አድልዎ አቤቱታ እንዴት ማቅረብ እችላለሁ?</u> እርስዎ ወይም ተማሪዎ በትምህርት ቤት ውስጥ ልዩነት/አድልዎ ወይም አድልዎ የተሞላበት ትንኮሳ ደርሶብኛል ብለው ካመኑ፣መደበኛ አቤቱታ የማቅረብ መብት አለዎት።ይህንን ቅጽ መሙላት ግዴታ ባይሆንም፣ሁሉም መደበኛ አቤቱታዎች የሚከተሉትን ማሟላት አለባቸው (a) በጽሑፍ መሆን አለባቸው እና (b) አድልዎ ፈጽመዋል ተብለው የሚታሰቡትን የተከሰቱ ድርጊቶችን፣ሁኔታዎችን ወይም ክስተቶችን በግልጽ ማስፈር አለባቸው።አቤቱታ ከማስገባትዎ በፊት፣ ያሳሰቦትን ጉዳይ ከልጅዎ ርዕሰ መምህር ወይም ከሲያትል ሕዝብ ትምህርት ቤቶች የእንባ ጠባቂ (Ombudsperson) ጋር በስልክ ቁጥር (206) 252-0529 በመደወል መወያየት ይችላሉ።

<u>አቤቱታ የት ነው የሚቀርበው?</u>
ተማሪዎች፣ወላጆች/አሳዳጊዎች እና የሕዝብ አባላት፤ፆታዊ ትንኮሳን ጨምሮ ከአድልዎ/ልዩነት ጋር የተያያዙ ማናቸውም ጥያቄዎች እና/ወይም አቤቱታዎች በቀጥታ ወደሚከተለው አድራሻ መላክ አለባቸው: Office of Student Civil Rights, Seattle Public Schools, MS 33-157, P.O. Box 34165, Seattle, WA 98124-1166፤ ኢሜይል: hreeoc@seattleschools.org ፣ ወይም ስልክ: 206-252-0306።

ሠራተኞች፤ፆታዊ ትንኮሳን ጨምሮ ከአድልዎ/ልዩነት ጋር የተያያዙ ማናቸውም ጥያቄዎች፣ ፍላጎቶች እና/ወይም አቤቱታዎች በቀጥታ ወደሚከተለው አድራሻ መላክ አለባቸው: Chief of Human Resources, Seattle Public Schools, Mailstop 33-157, P.O. Box 34165, Seattle, WA 98124-1166፤ ኢሜይል: hreeoc@seattleschools.org ወይም ስልክ: 206-252-0024።

<u>ቅሬታዬ በምስጢር ይያዛል?</u> ምስጢራዊነት ሙሉ በሙሉ የተጠበቀ እንደሚሆን ዋስትና መስጠት አይቻልም። የቀረቡትን የአቤቱታ ክሶች በተገቢው ሁኔታ ለመመርመር፣የአቤቱታ አቅራቢውን እና/ወይም የተማሪውን ማንነት ማሳወቅ ሊያስፈልገን ይችላል።መረጃዎችን ለአቤቱታዎ ምርመራ እና እልባት በጣም አስፈላጊ ናቸው ተብለው ከሚታሰቡት ሰዎች ጋር ብቻ በማጋራት፣የቀረበውን ማንኛውንም መረጃ ምስጢራዊነት በተቻለ መጠን በከፍተኛ ሁኔታ ለመጠበቅ እንሞክራለን።አንድ ሰው ቅሬታ ቢያቀርብም እንኳ፣ቅሬታ የቀረበበት ሰው ስለ ጉዳዩ የማወቅ መብት

አለው።በዚህም ምክንያት፣የትምህርት ዲስትሪክቱ የቅሬታውን ዝርዝር መረጃዎች ለተከሳሹ ማጋራት ሊያስፈልገው ይችላል።ቅሬታ የቀረበበት ሰው ስለ ጉዳዩ እንዳያውቅ መፈለግ፤መደበኛ ቅሬታዎን ተከታትለን ምላሽ ለመስጠት፣ምርመራ ለማድረግ እና ችግሩን ለመፍታት በምናደርገውን ጥረት እንቅፋት ሊሆንበት ይችላል።ስም-አልባ ቅሬታዎች በዲስትሪክቱ የአድልዎ ቅሬታ አሰራር መሰረት እንደ መደበኛ ያልሆኑ ቅሬታዎች ይቆጠራሉ።

<u>በቀል የተከለከለ ነው?</u> አዎ።ማንኛውም ሰው ቅሬታዎን ስላቀረቡ በእርስዎ ላይ የበቀል እርምጃ መውሰድ የዲስትሪክቱን ፖሊሲ ይቃረናል።ዲስትሪክቱ ቅሬታ አቅራቢዎችን እና ምስክሮችን ለመጠበቅ የፀረ-በቀል ድንጋጌዎችን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ያደርጋል።

መመሪያዎች

እባክዎ ቅሬታዎን በጽሑፍ ያቅርቡ **ወይም** ይህንን ቅጽ ይሙሉ፤ስለ ተከሰተው ድርጊት (ድርጊቶች) ሲያብራሩ በተቻለ መጠን ዝርዝር መረጃዎችን ይጥቀሱ።ድርጊቱ የተፈጸመበትን ቀን (ቀናት)፣የተከሰተውን ድርጊት (ድርጊቶች)፣በጉዳዩ ውስጥ የተሳተፉ ሰዎችን ስም እና የድርጊቱ ምስክር ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎችን ስም ያካትቱ።ቅሬታዎን ለመጻፍ በዚህ ቅጽ ላይ ባለው ቦታ ብቻ መወሰን የለብዎትም።ጉዳዩን በፍጥነት ለመፍታት የሚረዱ ተጨማሪ ወረቀቶችን ወይም ማስረጃዎችን አያይዘው ማቅረብ ይችላሉ።

ቅሬታዎችን ወደሚከተለው ያቅርቡ: የትምህርት ቤትዎ ርዕሰ መምህር፤ወይም በኢሜል ወደ: OSCR@seattleschools.org ይላኩ (ሠራተኞች ወደ HREEOC@seattleschools) ይላኩ ወይም በአካል ወደ: Seattle Public Schools, 2445 3rd Ave. S, Seattle, WA 98134 ያድርሱ ወይም በፖስታ ወደ: Office of Student Civil Rights/Human Resources, MS 33-157; P.O. Box 34165, Seattle, WA 98124-1165 ይላኩ።

የግል መረጃ (እባክዎ ይፃፉ):

ስም: የአያት ስም:

የስልክ ቁጥሮች: (የቤት)..
(የስራ/ሞባይል ስልክ)

ኢሜይል:

የቤት አድራሻ: ጎዳና:

ከተማ: ስቴት: ዚፕ ኮድ:

እርስዎ -
☐ ወላጅ/አሳዳጊ በራስዎ እና/ወይም በተማሪዎ ስም

☐ ሠራተኛ ☐ ተማሪ

☐ ሌላ አዋቂ

የአድልዎ ቅሬታ አይነት (እባክዎን በሚመለከትዎት ሁሉ ምልክት ያድርጉ):
አድልዎው የተመሠረተው:
ጾታ ☐ ጾታዊ ትንኮሳ፣ጾታዊ ጥቃትን ጨምሮ ☐ እምነት ☐ ቤት-አልባነት☐
ዘር ☐ የቆዳ ቀለም ☐ ሃይማኖት ☐ ብሔራዊ መነሻ ☐ አካል ጉዳተኝነት ☐ የአእምሮ እድገት ልዩነት (Neurodivergence)☐ ጾታ ☐ ጾታዊ ዝንባሌ ☐ ጾታዊ ማንነት ☐
እርግዝና ☐ የጋብቻ ሁኔታ ☐ አካላዊ ገጽታ ☐ የአገልግሎት እንስሳ መጠቀም ☐ ዕድሜ ☐ የወታደራዊ አገልግሎት ሁኔታ ☐ የትውልድ ሃረግ ☐ የጾታ መግለጫ ☐ ብሄር ☐ የስደት ወይም የዜግነት ሁኔታ ☐
ሌላ ዓይነት ትንኮሳ ☐

የበቀል እርምጃ ☐

አድልዎ/ትንኮሳ/ጥቃት/የበቀል እርምጃ ተፈጽሟል ተብሎ የሚታሰብበት ቀን:

የመጀመሪያው ቀን: የመጨረሻው/የቅርብ ጊዜው ቀን:

ይህ ድርጊት አሁንም እየቀጠለ ነው? ☐

<u>አድልዎ፣ ትንኮሳ፣ የአጸፋ እርምጃ ወይም ማስፈራራት/ማንገላታት ፈጽመዋል የተባሉ ሰው (ሰዎች):</u>

ስም: ትምህርት ቤት/ዲፓርትመንት:

ስም: ትምህርት ቤት/ዲፓርትመንት:

ስም: ትምህርት ቤት/ዲፓርትመንት:

<u>የቅሬታዎ መግለጫ/ማብራሪያ:</u>

እባክዎ ስማቸው በተጠቀሰው ሰው (ሰዎች) ላይ ያለዎትን ቅሬታ ያብራሩ።እርስዎ ወይም ልጅዎ በዘር፣በቆዳ ቀለም፣ በሃይማኖት፣በትውልድ ሐረግ፣በብሔራዊ ማንነት፣በኢኮኖሚ ደረጃ (በገቢ)፣በጾታ፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በጾታ መገለጫ (Gender identity)፣በእርግዝና፣በትዳር ሁኔታ፣በገጽታ (በአካል ገጽታ)፣ወይም በአእምሮ፣በአካል ወይም በስሜት ሕዋሳት አካል ጉዳተኝነት ምክንያት ምን ዓይነት አድልዎ እንደደረሰቹ? ወይም ከሌሎች በተለየ ሁኔታ እንዴት እንደተስተናገዳችሁ እባክዎ በዝርዝር ይግለጹ።እባክዎ ቅሬታ እንድታቀርቡ ያደረጋችሁን ድርጊት፣የተሰነዘሩ አስተያየቶችን ወይም የተከሰቱ ሁኔታዎችን ያብራሩ።ካስፈለገ ተጨማሪ ገጾችን አያይዘው ማቅረብ ይችላሉ።

እባክዎ ቅሬታዎን/አቤቱታዎን ያሳወቋቸውን ሁሉንም የዲስትሪክት ሠራተኞች ይለዩ (ስም ይጥቀሱ):

ሪፖርት የተደረገለት ሰው (ስም): ሪፖርት የተደረገበት ቀን:

ቅሬታው እንዴት እንደቀረበ ያብራሩ (ለምሳሌ: በኢሜይል፣በስልክ፣በአካል):

ውጤት/የተሰጠ ምላሽ:

ሪፖርት የተደረገለት ሰው (ስም): ሪፖርት የተደረገበት ቀን:

ቅሬታው እንዴት እንደቀረበ ያብራሩ:

ውጤት/የተሰጠ ምላሽ:

ሪፖርት የተደረገለት ሰው (ስም): ሪፖርት የተደረገበት ቀን:

ቅሬታው እንዴት እንደቀረበ ያብራሩ:

ውጤት/የተሰጠ ምላሽ:

ከላይ ስለተገለጹት ድርጊቶች መረጃ ሊኖራቸው የሚችሉ ሰው/ሰዎች:

(እነዚህ ሰዎች ድርጊቱን (ድርጊቶቹን) የተመለከቱ ወይም ስለ ሁኔታው መረጃ ያላቸው ናቸው።ካስፈለገ እባክዎ ተጨማሪ ስሞችን አያይዘው ያቅርቡ።)

ስም:

ከእርስዎ ጋር ያላቸው ግንኙነት (የሥራ ባልደረባ፣ተማሪ መምህር፣ወዘተ):

ከታወቀ፣ የስልክ ቁጥር: ኢሜይል:

ስም:

ከእርስዎ ጋር ያላቸው ግንኙነት:

የስልክ ቁጥር: ኢሜይል:

<u>የዕርቅ/የሽምግልና አማራጭ:</u>

ቅሬታዎን ለመፍታት ዕርቅን/ሽምግልናን እንደ አንድ ዘዴ ለመጠቀም ፈቃደኛ መሆንዎን ወይም ስለ ዕርቅ አማራጮች ተጨማሪ መረጃ መፈለግዎን እባክዎ ያመልክቱ:

አዎ ☐ አይሆንም ☐ ስለ ዕርቅ አማራጮች ተጨማሪ መረጃ እፈልጋለሁ☐

<u>ሌሎች መረጃዎች</u>

ለተማሪዎች፣ለወላጆች/ለሕጋዊ አሳዳጊዎች እና ለማንኛውም የኅብረተሰብ ክፍል:የተማሪዎች ሲቪል መብቶች ቢሮ (Office of Student Civil Rights) ሠራተኞች ለቀረቡት ቅሬታዎች ምላሽ የመስጠትና የመፍታት ኃላፊነት ይኖርባቸዋል።ለሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ሠራተኞች: የሰው ሀብት አስተዳደር ክፍል (Human Resources Department) ሠራተኞች ቅሬታዎችን ተከታትለው የመጨረሻ መፍትሄ የመስጠት ኃላፊነት ይኖርባቸዋል።ቅሬታዎን ለመፍታት ምርመራ ሊደረግ ወይም እንደ ዕርቅ ያሉ ሌሎች የሰላም አማራጮች ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ።ምርመራ ከተጀመረ ግን፣ጉዳዩን ለመፍታት እንዲቻል እርስዎን እና በቅሬታዎ ላይ የገለጿቸውን ሰዎች ለቃለ-መጠይቅ ማነጋገር ሊያስፈልግ ይችላል።ዲስትሪክቱ እንደ አስፈላጊነቱ፣በምርመራው ሂደት ሌሎች ሰዎችን የማነጋገር ሙሉ መብት አለው።

ምስጢራዊነት ሙሉ በሙሉ እንደሚጠበቅ ዋስትና መስጠት አይቻልም።የሰጡትን መረጃ ሁሉ በተቻለ መጠን ምስጢርነቱን ለመጠበቅ እንሞክራለን፤መረጃው የሚጋራው ቅሬታዎን ለመመርመርና ውሳኔ ለመስጠት የግድ አስፈላጊ ከሆኑ ሰዎች ጋር ብቻ ይሆናል።ቅሬታ የቀረበበት ሰው ራሱን የመከላከል ሕጋዊ መብት ስላለው፣ዲስትሪክቱ ስለ ቅሬታው ያለውን መረጃ በሙሉ ለተከሳሹ እንዲሰጥ ሊገደድ ይችላል። ማንነትዎ ለተከሳሹ እንዳይነገር ወይም በምስጢር እንዲያዝ ከጠየቁ፣ይህ የምስጢራዊነት ወይም የማንነት አለመግለጽ ጥያቄ በምርመራው ሂደት ላይ በሚጥለው ገደብ ምክንያት ዲስትሪክቱ ለቅሬታዎ እርስዎ በሚፈልጉት ደረጃ አጥጋቢ መፍትሔ እንዳይሰጥ ሊያደናቅፈው ይችላል።

ቅሬታ ስላስገቡ በእርስዎ ላይ የአጸፋ እርምጃ (በቀል) መውሰድ፣ወይም በምርመራ ሂደት በተሳተፉ ሰዎች ላይ ተመሣሣይ የአጸፋ እርምጃ መውሰድ ከዲስትሪክቱ መመሪያና ፖሊሲ ውጭ ነው።ቅሬታ በማቅረብዎ ምክንያት የአጸፋ እርምጃ (በቀል) ደርሶብኛል ብለው የሚያምኑ ከሆነ፣እባክዎ ወዲያውኑ ለትምህርት ቤቱ ርዕሰ-መምህር ወይም ለተማሪዎች ሲቪል መብቶች ቢሮ (Office of Student Civil Rights) ያሳውቁ።

ይህን ቅሬታ ከማቅረብዎ በተጨማሪ፣ተመሳሳይ ቅሬታን እንደ ለአካባቢዎ የሕግ አስከባሪ አካላት (ፖሊስ)፣የዋሽንግተን ስቴት የሕዝብ ትምህርት ዋና የበላይ ተመልካች ቢሮ (OSPI) ወይም የአሜሪካ የትምህርት መምሪያ የሲቪል መብቶች ቢሮ (OCR) ላሉት ሌሎች ውጫዊ ተቋማት የማቅረብ መብት አለዎት።ተመሳሳይ ቅሬታን ለሌላ አካል ወይም ፍርድ ቤት አስቀድመው

አቅርበው ከሆነ፣ዲስትሪክቱ ቀደም ብሎ የቀረበው ቅሬታ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ የራሱን ምርመራ ለጊዜው ሊያቆይ (ሊያራዝም) ይችላል።

ሙሉውን የአድልዎ ቅሬታ ሂደት እዚህ ድህረ ገጽ ላይ ማግኘት ይችላሉ:
https://www.seattleschools.org/wp-content/uploads/2021/08/3210SP.pdf

ለትምህርት ቤቱ ርዕሰ-መምህር መስጠት ወይም በኢሜይል ወደ: OSCR@seattleschools.org (ሠራተኞች :HREEOC@seattleschools.org) መላክ ወይም በአካል ወደ: Seattle Public Schools, 2445 3rd Ave. S, Seattle, WA 98134 ማድረስ ወይም በፖስታ ወደ: Office of Student Civil Rights/Human Resources, MS 33-157; P.O. Box 34165, Seattle, WA 98124-1165 መላክ።